# ኣለመታደል!



ሚስቴ፦
ኣንድ ጎረምሳ ውሽማ ወሽማ፣
ታምማ
በእኔ ላይ ለግማ፣ ጠምማለች
ያልታደለች!

እህቴ፦
የብድር ወርቅ ደቅድቃ፣
ደምቃ
በዕዳ ታንቃ፣ ትጨነቃለች፣
ያልታደለች!



እናቴ፦
የሰው ኩሕል ከዓይኗ ሽንቁራ
ታውራ፣
በደንቃራ ትደናቀፋለች፣
ያልታደለች!



ኣክስቴ፦
የዘጠኝ ወር ቅሪት ኣርግዛ፣
በምጥ ተይዛ
ከዚያ ተጋድማ ትሰቃያለች
ያልታደለች!

ወይኔ፦
ምን ላከብኝ ጋኔን፣ ኣረመኔ፣
መጥኔ!
በእውነቱ ያልታደልኩስ እኔ
እግዚኦ፣ ኩነኔ!

ገ/ኢ. ጕርፉ።

***Back to Meskot***

---

***The views reflected in the above poems are solely of the author and are not necessarily shared by** Meskot**. You may contact G.E. Gorfu for comments at** gegorfu@yahoo.com.*